የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ኤምባሲ
አቡዳቢ- የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች

سفارة جمهورية إثيوبيا الفيدرالية الديمقراطية
أبوظبي - الامارات

EMBASSY OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ABU DHABI-UAE

ቀን፡ ጥር 24 ቀን 2010 ዓ.ም
Date:
ቁጥር፡ ADEMB-04-2/053/10
Ref. No

ለመካከለኛው ምስራቅ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል
ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፤-ክቡር አምባሳደር ተበጀ በርሀ የሹመት ደብዳቤያቸውን ለተ.አ.ኤ. ለምክትል ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትር ማቅረባቸውን ስለማሳወቅ፣

በተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ሆነው የተሾሙት ክቡር አምባሳደር ተበጀ በርሀ የሹመት ደብዳቤያቸውን እ.ኤ.አ ጀነዋሪ 31 ቀን 2018 ለተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትርና ለዱባይ ገዥ ሼክ ሙሐመድ ቢን ራሺድ ቢን መክቱብ አቅርበዋል፡፡

ክቡር አምባሳደር ከዚህ በፊት የሹመት ደብዳቤያቸውን ቅጂ ለተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች የውጭ ጉዳይ እና ዓለም አቀፍ ትብብር ሚኒስቴር አንደር ሴክሬታሪ ለሆኑት ክቡር ሚ/ር አህመድ ሳሪ አል ማዝሩይ ያቀረቡ ሲሆን ጥር 23 ቀን 2010 ዓ.ም የሹመት ደብዳቤያቸውን ዋና ለምክትል ፕሬዝዳንትና አቅርበዋል፡፡ በዕለቱ ከክቡር አምባሳደር ተበጀ ጋር በተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች አምባሳዳር ሆኖ አዲስ የተሹሙት የቱኒሲያ ፣ የሊባኖስ እና የቡልጋሪያ አምባሳዳሮች የሹመት ዳብዳቤያቸውን ለምክትል ፕሬዝዳንቱ አቅርበዋል፡፡

ክቡር አምባሳደሩ የሹመት ደብዳቤያቸውን ባቀረቡበት ወቅት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ እና የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች የረጅም ጊዜ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን በልማት ትብብር ፣ በኢንቨስትመንት እና ንግድ ዘርፍ ያላቸው ግንኙነትም እያደገ መምጣቱን አምባሳደር ተበጀ በዚሁ ወቅት ገልፀዋል። በተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች ቆይታቸው የሁለቱን አገራት ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የተቻላቸውን ለማድረግ ቁርጠኛ መሆናቸውን ገልጸው ለዚህ ስኬት ድጋፋቸውን ጠይቀዋል፡፡ የሁለቱን አገራት ዲፕሎማሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚሰሩም አምባሳደር ተበጀ ገልጸዋል።

ከሠላምታ ጋር

Tebeje Berhe
ተበጀ በርሀ
አምባሳደር

ግልባጭ:-

- ለቃል -አቀባይ ጽ/ቤት
- ለፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል
  ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
  አዲስ አበባ

☎+971-2 665 5111 🖷 +971-2 666 0096 ✉ 63795 email: ambassador.abudhabi@mfa.gov.et, abudhabiethiopianemb@gmail.com
Vila 119, Al Qasbah street, Near Al Bateen Majlis and old Municipality, Al Bateen Abu Dhabi, UAE

# ዜና

## ክቡር አምባሳደር ተበጀ በርሀ ለተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች ምክትል ፕሬዝዳንት፣ጠቅላይ ሚኒስትርና ዱባይ ገዥ የሹመት ደብዳቤያቸውን አቀረቡ፣

››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››››

በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ሆነው የተሾሙት ክቡር አምባሳደር ተበጀ በርሀ የሹመት ደብዳቤያቸውን እ.ኤ.አ ጀነዋሪ 31 ቀን 2018 ለተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትርና ለዱባይ ገዥ ሼክ ሙሐመድ ቢን ራሺድ ቢን መክቱብ አቅርበዋል፡፡

ክቡር አምባሳደሩ የሹመት ደብዳቤያቸውን ባቀረቡበት ወቅት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ እና የተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች የረጅም ጊዜ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ያላቸው ሲሆን በልማት ትብብር ፣ በኢንቨስትመንት እና ንግድ ዘርፍ ያላቸው ግንኙነትም እያደገ መምጣቱን አምባሳደር ተበጀ በዚሁ ወቅት ገልፀዋል። በተባበሩት ዓረብ ኤሚሬቶች ቆይታቸው የሁለቱን አገራት ግንኙነት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ የተቻላቸውን ለማድረግ ቁርጠኛ መሆናቸውን ገልጸው ለዚህ ስኬት ድጋፋቸውን ጠይቀዋል፡፡ የሁለቱን አገራት ዲፕሎማሲያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚሰሩም አምባሳደር ተበጀ ገልጸዋል።